ግብፅን ለመቆጣጠር የተደረገ የመጨረሻ መከራ

የየሩሳሌሙ ንጉስ አል-ማሪክ ሁሉንም ወታደሮች ከግብፅ ባለማስወጣት ስምምነቱን አፈረሰ። የሶሪያ ወታደሮች ተጠቃለው ከወጡ በኋላ ግብፅን ለመውረር አትዶ ነበር። ቀድመው በተዘጋጁት መሠረት የቡልቤይስን ከተማ ከያዙና ብዙ ሰዎችን ከገደሉ በኋላ ወደ አል-ፋስታት አቀኑ። ገሸርው ሻዊር መስቀለኞች አል- ፋስታትን ለመያዝ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ተነገረው። ሻዊር ለአምሳ አራት ቀናት ያህል አል-ፋስታትን ከመስቀለኞች ተከላከለ። በመጨረሻ መስቀለኞች አል-ፋስታትን በመተው ወደ ካይሮ ሊዱና ዙሪያዋን ከበቧት። ሻዊር ተመልሰው እንዲመጡ የላከባቸው የሶሪያ ወታደሮች ተመልሰው እስኪደርሱለት ድረስ ከመስቀለኞች ጋር ሲደራደር ቆየ።

ኑረዲን ግብፅን ለመያዝ የመጣለትን ዕድል ተጠቀመበት። ለሦስተኛ ጊዜ በአሰዱዲንና በሳላሃዲን የሚመራ ሌላ ጦር ላከ። ኑረዲን የላከው ጦር ግብፅ ደርሶ ከግብፅ ጦር ጋር የተቀላቀለ ጊዜ መስቀለኞች ያለምንም ግጭት ግብፅን ለቀው ወጡ።

ሺርኩህ ካይሮ ሲደርስ ህዝቡ በደስታ ተቀበለው። የመልካም ዕድል ምልክት አድርገው ተመልክተውት ነበር። የፋጢሚዮች ኸሊፋ አል-ዓዲድ ሞቅ ባለ አቀባበል ከጎኑ አደረገው። በሻዊር ላይ የተጠነሰሰ የግድያ ሴራ ነበር። በ564 (እ.ሐ.አ) ሻዊር ተገደለ። አሰዱዲን የፋጢሚዮች ኸሊፋ የበላይ ገዥ በመሆን የሻዊርን ቦታ ያዘ። ነገር ግን ከሁለት ወራት በላይ አልቆየም ነበር። በዚያው ዓመት (1169 እ.ኤ.አ) በሞት ተለየ።

ትንተና እና አስተያየት

ከአሳቱ ጋር የነበረውን ውስና የተሳተፋባቸውን ጦርነቶች ስንመለከት ሰላሑዲን ጀግንነትን፣ በፈተናዎችና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ብስለትን፣ በጦርነት ስልቶች ደግሞ ከሀሉትን አጣምሮ የያዘ ልዩ ስብዕና ነበረው ብለን መደምደም እንችላለን። ገና በለጋ ዕድሜው በታሪክ ውስጥ ልዩ እና ታላቅ ሰው እንደሚሆን ያስታውቅ ነበር። እርግጥ ነው የተሰለፈባቸው ጦርነቶች ልምዱን፣ በራስ መተማመኑን እና ኢማኑን

ጨምረውለት አልፈዋል። አስከዛሬ ድረስ በታሪክ ላይ ነግሶ የኖረው ድንንቱ በግልፅ የታየባቸው መድረኮች ሦስት ነበር።

ስላሉዲን የመስሊም አገሮችን እንዲት ወደ ፖለቲካዊ አንድነት ማምጣትና አንድ ኢስላማዊ ግንባር መፍጠር ቻለ? የሚለውን ጥያቄ በሚቀጥለው ምዕራፍ ለማየት እንሞክራለን። አስከዛሬ ድረስ ታሪክ የሚጠቅሰው፣ ለመሬኒው ትውልድ በሙሉ አርአያ ሆኖ የቀረውና የመስቀልኞች ወኔ የተሰለበት የሒትቲን ጦርነት ድል ከተገኘባቸው ወሳኝ ምክንያቶች መካከል አንዱ ይኸው ተግባሩ ነበር።

ምዕራፍ ሦስት

ሰላሑዲን በግብዕ ውስጥ

የፋጢሚዮች ኸሊፋ ዋና ገኘ

አሰዱዲን ሺርኩህ ከሁለት ወራት የመሪነት ሚናው በኋላ በመሞቱ ምክንያት ሰላሑዲን ለሦስት ቀናት ሐዘን ተቀመጠ። ከዚያም ምንም እንኳ ሰላሑዲን በዕድሜው ገና ለጋ ወጣት ቢሆንም በጊዜው ግብዕ ውስጥ በርካታ ታላላቅ ስብዕናዎች፣ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እና የጦር መሪዎች ቢኖሩም የፋጢሚዮቹ ኸሊፋ አል-ዓዲድ ግን ሰላሑዲንን የመንግስቱ ዋና ገኘ እንዲሆን መረጠው። ታሪክ ፀሐፊዎች የዚህን ምርጫ ምክንያት ሲገልፁ፡- ሰላሑዲን ገና ወጣት ስለሆነ በቀላሉ መቆጣጠር እችላለሁ እንዲሁም ለምፈልገው ዓላማና ጥሪ ሳያንገራግር ምላሽ የሚሰጥ መዳፌ ላይ የተቀመጠ ኃይል ይሆነኛል በማለት የፋጢሚዮቹ ኸሊፋ ተስፋ አድርጎ ስለነበረ ነው ይላሉ። ነገር ግን ዕጣ ፈንታ ሌላ የራሷ ውሳኔ እንደነበራት ኋላ ላይ እናያለን።

ሰላሑዲን ለዚህ ትልቅ ኃላፊነት ሲመረጥ ገና የሰላሳ ሁለት ዓመት ወጣት ነበር። ይሁን እንጂ ስለጦርነት ጉዳዮች ከኑረዲንና ከአጎቱ ሺርኩህ ብዙ ተምሮ ነበር። ሁለቱ ሰዎች ለሰላሑዲን ልቅና ዋና ምክንያቶች ነበሩ ማለት ይቻላል።

ሰላሑዲን የግብዕን ህዝብ ፍላጎት ለማርካት ጥረት ማድረግ ጀመረ። በገንዘብ አንበሸበሻቸው። ከግብዕ መኳንንቶች ጋር ተባብረው እንዳይነሱበት ለማድረግ በመልካም ሁኔታ ያዛቸው። በመሆኑም እጅግ ወደዱት፣ ከልባቸው ቀረቡት። በተጨማሪም ፍራንኮች ላይ የተቀዳጃቸው ድሎችና ደሚታን፣ ጋዛን እና ዓቃባህን ከፍራንኮች ነፃ ማውጣቱ ዝናውን አደመቀለት። ግብፃዊያኑ ሐጅ ለማድረግ ወደመካ በሚያደርጉት ጉዞ የቀይ ባህር መግቢያ በር ሁኖ ሲያገለግላቸው የነበረውን የዓቀባህ ባህር በር ነፃ በማውጣት ያገኘው ትልቅ ድልና መንፈሳዊ ተጓዦችን ሊገጥሟቸው ከሚችሉ አደጋዎች በመጠበቅ በኩል የነበረው ቁርጠኝነት፣ በእሱና በግብፃዊያኑ መካከል ለተፈጠረው ፍቅርና መተማመን ትልቅ አስተዋፅኦ ነበራቸው። ግብፃዊያኑ የሺዓ ተከታይነታቸውን ትተው

የሱኒዩ ዓለም አነሳል መሆናቸውና ከሰላሑዲን ጋር በመሆን የአነሰና የአላህ ጠላቶችን ለመፋለም ጉርጠው መነሳታቸው የኖረቶቹ ተፈጥሯዊ ውጤቶች ነበሩ።

የውስጥ ሴራዎች ማብቃት

ሰላሑዲን ሥልጣነ መንበሩን ሲያዝ በአናሳ የወጣትነት ዕድሜ ላይ ይገኝ እንደነበር መነሻሳችን ይታወሳል። በዚህ ምክንያት በፋጢማይድ መንግሥት ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች ተመቀኙት። መብታቸውን ለነጥቅ የመጣ ወንረ ልውጥ አድርገው ተመለከቱት። የትኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ከፍለው ሥርወ-መንግሥቱ ግብፅ ውስጥ የነበረውን ሻርማ ሞገስና ኃይል መመለስ እንዳለባቸው በማሰብ ሩቅ አሳቢ የሆነውን ወጣት መሪ ለማስወገድ መዶለትና ማሴር ጀመሩ። ከሁሉም ሴራዎች በላይ ከባድ የነበሩት ግን የነጃህ ሴራ እና ለእሊፋው ቅርብ የነበሩት የዓማራህ አል-የማኒ እና የከንዙ-ደውላህ ሴራዎች ነበሩ።

የነጃህ ሴራ

ነጃህ በእሊፋው ቤተ-መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ነበረው። የፋጢማይድ ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻ እሊፋ በሆነው በአል-ዓዲድ አንድ ቤተ-መንግሥት ውስጥ ተቀምጦ በግብፃዊያን ከተደራጀ አንድ ቡድን ጋር በመተባበር በሰላሑዲን ላይ ማሴር ጀመረ። የፍራንክ አጋር በመሆን ሰላሑዲንን ለማስወገድ አቀደ። እሐአ 564 መስቀለኞች ወደ ግብፅ እንዲዘምቱ ለመጠየቅ መልዕክተኛ ላከ። መስቀለኞች ግብፅ ደርሰው ከሰላሑዲን ጋር በሚዋጉበት ጊዜ ሰላሑዲንን ከጀርባ ለማነቃትና በሁለት ሠራዊቶች መካከል አስገብቶ ለመደምሰስ አቅዶ ነበር።

እቅዱን አጠቃሎ ከሣፊ በኃላ ከአዲስ ጫማ ውስጥ አስቀመጠና መልዕክቱን ለፍራንክ እንዲያደርስ ለአንድ ሰው ሰጠው። ነገር ግን ጫማው ከሰላሑዲን ደጋፊዎች እጅ ገባ። በፍጥነት ለሰላሑዲን አስረከቡት። ሰላሑዲን እውነቱን ካረጋገጠ በኃላ ምንም እንዳልተፈጠረ ለማስመሰል ወሰነ። የነጃህ ተከታዮችና ደጋፊዎች እንዲነሰብት ስላልፈለገ

የደረሰውን መረጃ በሚስጥር መያዙን መረጠ። ነጃህን የሚተካበት ትክክለኛው ጊዜ እስኪመጣ ድረስ በትዕግስት ለመጠበቅ ወሰነ።

አንድ ቀን ነጃህ ከካይሮ ውጪ ወደሚገኘው የራሱ በተ-መንግስት ለመሔድ በወጣበት አጋጣሚ ሰላሑዲን ወታደሮቹን ላከበት። ነጃህ ተገደለ። የነጃህን መገደል ተከትሎ የኸሊፋው ሠራዊት አባል የሆኑ 50.000 ሱዳናዊያን ወታደሮች ሰላሑዲንን ለመበቀል ተዘጋጁ። ሰበቀል በቋመጡ ወታደሮችና በሰላሑዲን መካከል ሁለት ቀን የፈጀ ጦርነት ተደረገ። ሰላሑዲን አሸነፈና ነጃህን ብቻ ሳይሆን ያመፁበትን ሱዳናዊያን ወታደሮችንም ተገላገላቸው።

በእርግጥ ያመፁበት ሱዳናዊያኖቹ ወታደሮች ብቻ አልነበሩም። ፋቢሚይ መሃንንቶችም የጦርነት እሳት ሲያቀጣጥሉና መንግስቱን ከውስጥ ሲነጩት ነበር።

የኢማራህ አል-የማኒ ሴራ

ሰላሑዲንን ለማጥፋት ከተወጠኑ ትላልቅ ሴራዎች ውስጥ አንዱ በታዋቂው ታሪክ ዘጋቢ በኢማራህ አል-የማኒ የተመራው ሴራ ነበር። ካይሮ ውስጥ በርካታ ሰዎችን ሰበሰበና ከአል-ዓዲድ ወንድ ልጆች መካከል አንዱን እንዲመርጡና ሰላሑዲንን በማባረር የፋቢሚዮችን መንግስት እንዲመልሱ አማባቸው። የሰላሑዲንን መንግስት በመደምሰስ እንዲተባበሯቸው ለመጠየቅ በፍጥነት ወደ ፍራንክች መልዕክተኛ ላከ። በጣም ብዙ በጥላቻ የተሞሉ ክፉ ሰዎችን ከጎኑ ማሰለፍ ችሎ ነበር።

ከሴረኞች ውስጥ አንዱ የነበረው ዘይኑዲን ነጃህ ከሰላሑዲን ሊያገኘው የሚችለውን ትልቅ ሽልማት በማሰብ ከዳቸው። ሰላሑዲን ሁሉንም ሰብስቦ አሰራቸው። በሃገር ላይ ተመሳሳይ ሴራ ለሚያስቡ ሁሉ ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ ሁሉንም በሞት ቀጣቸው። ይህ የሆነው እ.ሐ.አ በ569 ነበር።